# የቀረችውን ኢትዮጵያ ለማፍረስ የሻቢያ መሳሪያ እንዳንሆን እንጠንቀቅ !

ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን(ሱዳን)
ታህሳስ 29 ቀን 1998ዓ.ም.

አንደርዳሪ

ወያኔ የግንቦት 7ቱን 1997ዓ.ም ምርጫ ውጤት ቀምቶ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የወሰደው ጭፍጨፋ ሆነ የምርጫ ማጣራት የተባለውን ቧልት ኣጠናቀ አብላጫ ድምጽ ያገኘሁት እኔ ነኝ ብሎ መንግስት ከመሰረተ በኋላ እንኳ ቢሆን የተቃውማሚ ፓርቲዎች ሆኑም ህዝቡ በሰላማዊ ትግል ላይ የነበረው ተስፋ ከፍ ያለ ነበር። ህዝቡ ተቃዋሚዎች ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ የሰሯቸውን የቴክኒክ ስህተቶችን አርመው የተቀናጀና የተጠናከረ ህዝባዊና ሰላማዊ የተቃውሞ ትግል ጥሪ እንዲያደርጉ ተማጽኗል ። ይሁንና ተቃዋሚዎች ከተከፋፈሉ በኋላ ቅንጅት ለብቻው ለጠራው ሰላማዊ ተቃውሞ ወያኔ የወሰደው ፋሺስታዊ ጭፍጨፋ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ወደ ሌላ አደገኛ ጎዳና ነድቶታል። ዛሬ በብዙዎች ዘንድ ወያኔ ያለ ትጥቅ ትግል አይወድቅም የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ አድርጓል። ይህም የትጥቅ አማራጭ እንደገና ነፍስ ዘርቶ እንደዋነኛ የትግል አማራጭ እየቀረበ ያለበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል።

ስለ ትጥቅ ሲነሳ ደግሞ የኋላ ደጀን ፤ የትጥቅ አቅርቦት፤ ቁስለኛና በሽተኛ ማግለያና የመንደርደሪያ ቦታ ከሚነሱት ዋነኛዎቹ ናቸው። ለዚህ የትጥቅ አቅርቦትም ሆነ የኋላ ደጀንነና መንደርደሪያ ቦታ ሻቢያ እኔ አለሁላችሁ ካለ መጪው ግንቦት ድፍን ስምንት አመት ሊሞላው ነው። እንደሚፈልገው ባይሆንም ተንደርድረው በሻቢያ እቅፍ የገቡ አሉ። ትጥቅ ትግል እያደረግን ነው እያሉም ነው።

የትጥቅ ትግል አሁን ባለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የኢትዮጵያን ችግር ይፈታል ወይስ ያወሳስባል የሚለውን ተገቢና ወቅታዊ ጥያቄና ክርክር ለጊዜው እናቆየውና ለኢትዮጵያ አንድነት እንታገላለን የሚሉ ሃይሎች ከሻቢያ እርዳታ የመሻታቸውን ብልህነትን እንፈትሽ። አባባሉ «ላዋቂ አይመከሩም ለአንበሳ አይመትሩም» ቢሆንም ሁላችንም ከግርግርና ከስሜት ውጥተን ቀም ብለን አካሄዳችንን እንድፈትሽ ይህችን ደወል ለሁላችንም ደውልን።

ዲያቢሎስ መልሶ መልአክ መሆን አይቻለውም። ፈጣሪውን ክዶ እኔ ነኝ ፈጣሪ ብሏልና። የዲያቢሎስ ስራ እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ ሰዎችን ፈጣሪያቸውን ማስካድ ነው። ሻቢያም ኢሳይያስና መሰል ጸረ ኢትዮጵያ ተከታዮቹ እስካሉ ድረስ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከመማሰን ለዲቂቃም ወደኋላ አይመለስም። ለዚህ እማኝ ካስፈለገን የምንጠራው ራሱን ሻቢያን ነው። ኢትዮጵያን ማፍረስ ተልእኮው መሆኑን ደጋግሞ ነግሮናልና ። አድርጎም በተግባር አሳይቶናል። እያሳየንም ነው።

ጥያቄው ታዲያ አላማው ኢትዮጵያን ማፈርስ የሆነ ቡድን ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፈን ለሚታገሉ ኢትዮጱያዊ ሃይላት ይረዳል ተብሎ እንዴት ይታመናል ነው። ለኢትዮጵያ አንድነት ነው የምንታገለው የሚሉና የሻቢያን እርዳታ ለማግኘት ደጅ የሚጠኑ ለዚህ ጥያቄ አሳማኝ መልስ ሊሰጡን ይገባል። እኛ ግን ሻቢያና ወያኔ አንድም ሁለትም ናቸው የሚል እምነት ስላለን በዚህ ጽሁፍ የመጀመሪያ ክፍል ሻቢያን ተጠቅሞ ወያኔን መጣል አይቻልም የሚል ጽኑ እምነታችንን እናስረግጣለን። እናም ከሻቢያ ጋር እሰራለሁ ማለት «በሬ ሆይ ሳሩን እየህና ገደሉን ሳታይ» አይነት ነው ብለን ባንተርትም

እራስንም አገርንም ለእርድ ማዘጋጀት እንዳይሆን ስጋታችንን እናስተጋባለን። «በእባብ የተነደፈ ልጥ ባየቁጥር ይደነግጣል» እንዲሉ ነውና። በመጨረሻም «የለም ከሻቢያ መዳፍ ኢትዮጵያን የሚጠቅም ነገር ፈልቅቀን እናወጣልን» ካሉ ደግሞ በኢትዮጵያዊነታችን ማድረግ አለባቸው የምንለውን እንመክራለን።
እንቀጥል:-
የሻቢያን እርዳታ ተጥቅሞ ወያኔን መጣል ይቻላል የሚሉ ወገኖች ከሚያቀርቡት ዋነኛ ምክንያት «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ» የሚለው ብሂል ነው። ሌላ አሳማኝ ምክንያት ካላቸው ለማድመጥ ዝግጁ ነን። «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» የሚለው ብሂል ግን በዚህ ሁኔታ የተሳሳተና ያለቦታው የተጠቀሰ መሆኑን እናስረግጥ።

ሀ ግልጹን ግልጽ ለማድረግ ያህል
የሻቢያ አለማ ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። ሻቢያ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ስትጠፋ ኤርትራ የምትባል አገር ህልውናዋ የተረጋገጠ ይሆናል ብሎ ወጥኖ ለኤርትራ ነጻነትና በእግሯ መቆም የሚታገል የራሱን ሎሌ አሰልጥኖና አስታጥቆ የኢትዮጵያን በትረ ስልጣን ያስጨበጠ ነው። ወያኔን ከብሄረ ትግራይነት ወደ ሻቢያ ተቀጥላነት የለወጠ እጅግ አደገኛ ቡድን ነው። መለስ ዜናዊ፤ ኪዳኔ ጃማይካ፤ በረከት ስምዖን፤ እና መሰሎቻቸው ኢትዮጵያዊ ጭምብል አጥልቀው ከወዲ ኢሳይያስ አፈወርቂ ያላነሰ እንዲያውም በላቀ ደረጃ ለኤርትራ ህልውና የሰሩ ሻቢያዎች እንጂ ሌላ አይደሉም። ኢሳይያስ ስልጣን ሊይዝ ትንሽ ሲቀረው ለአንድ ጋዘጠኛ በሰጠው ቃለ ምልልስ « ኢትዮጵያ የምትባል አገር ከሥርና አስራ አምስት አመታት በኋላ አትኖርም። ለኢትዮጵያውያን የመቶ አመት የቤት ስራ ሰጥተናቼዋል። ጦርነቱን ወደ ደቡቡ ክፍል እንወስደዋለን ወዘተ » ያለውን ልብ ይሏል። የዛሬው የሻቢያ «ኑ ልርዳችሁ» አዛኝ ቅቤ አንጓች አይነት ጉድ ጉድ ያን ትንቢቱን ለመተግበር እንዲያመቸው በየቦታው እሳት ለመለኮስ ብቻ ነው። እስካሁን የኦሮሞን፤ የአማራ፤ የሲዳማ፤ የቤኒሻንጉል፤ የጋንቤላ፤ የሶማሌ ክልል( ኦጋዴንያ)፤ የትግሬ ጦር እያሰለጠነልን ነው። ይህ ሁሉ ሶስት አራተኛ ህዝቡ በምጽዋት በሚያኖረው በኢሳይያስ አይዞህ የሚባልና ጦር ሰንቆ ኢትዮጵያ ወደምትባል አገራችን የተሰማራ ወይም ሊሰማራ ወቅትና ጊዜ የሚጠብቅ ነው። ልብ ያላችሁ ልብ በሉ። ስለ ሻቢያና ወያኔ ብዙ የሰበከን አብርሃም ያየህም «በትግራይ ህዝብ ላይ ሊደርስ የሚችል ጥቃትን ለመከላከል» በሚል ማምታቻ ልዩ የትግራይ ጦር በሻቢያ ጉያ እያደራጀልን ነው። ሻቢያ ይህ አልበቃውም ወይም ኢትዮጵያን ለማተራመስ በቂ ሆኖ አላገኘውምና በጎረቤት አገር ኤምባሲ ወኪሎቹ ሆነ በአፍቃሪ ሻቢያ ደጋፊዎቹ አማካነት ሌሎች የአንድነት ሃይሎችም የሱን እርዳታ ለማግኘት ሰልፍ እንዲይዙ መወትወት ከጀመረ አመታት ቢያልፉም የዘንድሮው የወያኔ ሙሴሊኔዊ ጭፍጨፋና የህዝብ ፍጅት ግን ለጥሪው ልዩ ክበደት ሰጥቶለታል። በነገራችን ላይ በጭፍጨፋው የሻቢያ እጅ የለበትም ብሎ አፍን ሞልቶ መከራከርም አይቻልም።
የሻቢያ «ላስታጥቃችሁና ወያኔን በትጥቅ ትግል ጣሉ» የሚለው ተማጽኖ በአምስት የተለያዩ አስተሳሰብና አላማ ባላቸው ፖለቲከኞች ዘንድ ስሚ ሊያገኝ ይችላል።
1ኛ. «የሻቢያን ጸረ ኢትዮጵያዊነንት እናውቃለን ግን እንጠቀምበት» የሚሉ የአንድነት ሃይሎች፤
2ኛ. ለኢትዮጵያ አንድነት ሲሉ በቅንነትና በየዋህነነት ጥሪውን የሚቀበሉ፤
3ኛ. ኢትዮጵያ ብትፈርስም ብትኖርም ግድ የሌላቸው ፤
4ኛ. ቅጥረኞችና የውጭ ሃይሎች መጠቀሚያና አጀንዳ አራማጆች፤
5ኛ. የፖለቲካ ነጋዴዎች ተብለው ሊፈረጁ የሚችሉ ናቸው።
ለ. <u>ሻቢያ ወያኔ እንዲወድቅ አይፈልግም</u> ፡

በመጀመሪያ ሻቢያና ወያኔ ተጣልተዋል ወይ ? ቢጣሉስ እውን ሻቢያ ወያኔ በስልጣን ቢኖር ነው የሚጠቀመው ወይስ ቢወገድ ? ዛሬ ባለው ሁኔታ ሻቢያ ማለት ኢሳይያስ ወያኔ ማለት ደግሞ መለስ ዜናዊ ናቸው። እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በግል ስለመጣላታቸው የሚያውቁት እግዜርና ራሳቸው ብቻ ናቸው። በርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ነገር ቢኖር ግን ሁለቱም ለኤርትራ ህልውና አንዱ ከሌላው ያላነሰ አስተዋጾ ያደረጉና አሁንም በኤርትራ ጉዳይ ላይ በፍጹም የሚስማሙ መሆናቸውን ነው። በመሆኑም ሻቢያ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለመጣል ይታገላል የሚለው የተላላዎች ግምት ብቻ ነው። እውን ሻቢያ ቅንጅት፤ ወይ ህብረት ወይ መላው የኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ወይስ ኢህአፓ ወይም ሌላ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ስልጣን ቢዝይ ይሻለኛል ብሎ ያምናል ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ አሉታዊ ነው። የሻቢያን አላማ ለማራመድና ለማስፈጸም በድርጅት ከወያኔ፤ በግለሰብ ከመለስ ዜናዊ የተሻለ ሊኖር አይችልም። ሻቢያ ይህን ይስታል ብሎ ማሰብ ደግሞ ትልቅ ተላላነት ነው።

<u>ሐ ሻቢያ የተቃዋሚ ሃይሎችን «ኑ ላስታጥቃችሁ» ሲል እንደለመደው ልጠቀምባችሁ ማለቱ ነው!!</u>

ሻቢያ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ የሶሺያሊስት ርዕዮት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፋሽን በነበረበት ወቅት ለአገራቸው ቅን የሚያስቡ ወጣት ኢትዮጵያውን የብሄር ጭቆናን መቃወም በሚል ስበብ ሳያውቁ ኤርትራን የመገንጠል አላማውን አራምደውለት ነበር። «የኤርትራን ጥያቄ» አግባብነት ከሻቢያ ይልቅ የኢትዮጵያ የያኔ ተራማጅ ክፍል ይበልጥ ማስተጋባቱን ዛሬ በጸጸት የምናስታውሰው ነው። ሻቢያ ግን በስህተት እንኳ ለኢትዮጵያ አንድነት ሃይሎች አንዳች ጊዜም እርዳታ አላደረገም። ተጠቅሞባቸው የራሱን አገልጋይ ወያኔን ካጠናከረ በሀዋላ ሊያጠፋቸው ጣረ እንጂ። ለአብነት ያህል በሻቢያ ክልል ወደ አሲምባ ያለፈውን የኢህአፓን ጀማሪ ጦር አመት ሙሉ ማገቱንና ወያኔ ስልጣን ሊይዝ ሲቃረብ የኢህአፓን ጦር ከሱዳን መንግስትና ከወያኔ ጋር አብሮ መውጋቱን ልብ ይሏል። ሻቢያ ያኔ የኢትዮጵያ አንድነት ሃይልን ክፍፍልን በሚገባ እንደተጠቀመበት ሁሉ ያሁኑ ጥሪም ያን ለመድገም ነው። የሻቢያ ምሁራን የውሸት ታሪክ ጽፈው ኤርትራዊ ያሉትን ስነ ልቦና ሲፈጥሩ የኛዎቹ ያለ እውነተኛ ታሪካችንን መከላከል አልቻሉም። ፖለቲከኞቻችን አሻግሮ ማየት አቅቷቸው የእርስበርስ መጠላለፍን በማስቀደማቸው አብዮት በምርጥ መኮንኖች ብቻ ሳይሆን በገንጣይ አስገንጣዮች ተጠለፈና አሁን ላለንበት በቃን ። እናም ሻቢያ አሁን የተያዘውንና በሰላማዊ ትግል የተገኘውን ህዝባዊ መነሳሳት ሊያጨናግፍ ቢሯሯጥ የሚጠበቅ ነው። በኛ እምነት ከድሮ እስከዛሬ ለኢትዮጵያ ችግር አለመፈታት ትልቁ ድንቃራ የተቃዋሚዎች ህብረት ማጣት ነው። የወያኔ መውደቅ አለመውደቅ የሚውሰነውም ከሻቢያ መሳሪያ ማግኘትና ማጣት ሳይሆን በተቃዋሚዎች በሃቀኛ ህብረት ዙሪያ መሰባሰባና አለመሰባሰብ ነው።

በመሆኑም ወያኔ/መለስ ዜናዊ እና ሻቢያ/ኢሳይያስ አፈወርቅ በኤርትራ ጉዳይ ላይ አንድም ሁለትም ናቸው ካልን ሻቢያ ልርዳ ሲል ሊከፋፍል፤ ሊያዳክም ፤ ለወያኔ ዱላ ደህና አድርጎ ሲያመቻች፤ የኢትዮጵያ አንድነት ሃይል ከቁጥጥሩ እንዳይወጣና አስፈልጊ ሆኖ ካገኘው ከመለስ ዜናዊ ጋር መልሶ ሊደራደርበት ሲያደባ፤ ምናልባት መለስ ዜናዊ በህዝባዊ ሃይል ከወደቀም የራሱ አሻንጉሊት መንግስት ለመመስረት ነው። ከነዚህና መሰል መሰሪ አላማዎች ውጭ ሻቢያ ለኢትዮጵያ በጎ አሰበ ማለት ሰይጣን ተመልሶ መልአክ ሆነ ማለት ነው። የማይታሰብ ነው። ያለተፈጥሮው ውሃ ሽቅብ ፈሰሰ እንደማለትም ነው።

<u>የሻቢያን «ስጦታ እንጠቀምበት» ለሚሉ ምክር ቢጤ</u>

የኛ አቋም «ጠላት ወዳጅ ላይሆን አልለማመጥ» የሚለውን የአበው ምሳሌዊ አነጋገርን መሰረት ያደረገ ነው። ከጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ለኢትዮጵያ አንድነት የሚጠቅም ነገር ይገኛል ብለን አናምንም። ይሁንና ሻቢያን በመጠቀም ለኢትዮጵያ አንድነት እንታገላለን የሚሉ

ሃይሎች በአቋማቸው ከጸኑ መሳሳታቸውን ብናውቅም አቋማቸውን እናከብራለን። ያም ሆኖ አገራችን የሚሏት አገራችን በመሆኗና አብረዋቸው ሊሰለፉ የሚችሉም ኢትዮጵያዊ ወገኖችቻን በመሆናቸው፤ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ እንዲያደርጉ አደራ እንላለን።

1ኛ. ከሻቢያ ጋር በምን አይነት አገራዊ ጉዳይ ላይ መደራደር አይጠበቅባቸውም። ሻቢይ ኤርትራን እንደሃገር እወቁልኝ ከሚለው ጀምሮ ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ተጽእኖ የሚኖረው ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ቢደራደሩ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣

2ኛ. በእርግጥ ሻቢያ ሊረዳቸው ከፈለገ እርዳታውን ከኤርትራ መሬት ውጭ መስጠት እንዳለበት፣ ይህም ሻቢያ የማይታመን በመሆኑና አመራርንም ሆነ ሌሎች የሰው ሃይልን የሚያግት ሲፈልግ የሚያስርና የሚገል ነፍሰ ገዳይ ቡድን በመሆኑ ነው። ይህን ትናትም ያደረገው ዛሬም እያደረገው ያለ በመሆኑ ነው።

3ኛ. ሻቢያ እስካሁን ድረስ አስሮ የሚያሰቃያቸውን የቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ሃይል አባላት በቅድሚያ እንዲፈታና የሌሎቹንም በጁ የገቡትን መዳረሻ እንዲያስውቅ፣ ሻቢያ አለማቀፍ ህግ ቢገዛው ኖሮ ስልጣን ከያዘ ከ15 አመታት በኋላ በምርኮነት በእጁ የገቡና ከሱዳን አፍኖ የወሰዳቸውን የጦር መኮንኖችን መዳረሻ አጥፍቶ የግዳጅ የጉልበት ሰራተኞች አድርጎ ምድራዊ ሰቆቃ መፈጸሙን ያቆም ነበር። ከነዚህ መኮንኖች መሃል ኮ/ል አይቼው አስማረ፤ሌ/ኮ ይርዳው ተሻለ፤ ኮ/ል አቦሻ ቦቦሻ፤ ኮ/ል አባተ ሳህሌ፤ ኮ/ል አለሙ ይርዳው፤ ሻለቃ ታምራት ከርሴ፤ ኮ/ል ግርማ ታደሰ፤ ኮ/ል ተሾመ ደስታ፤ ኮ/ል ንጉሴ ብርሃኑ ወዘተ ይገኙባቸዋል።

4ኛ. በምንም ጉዳይ ይሁን በምን በውስጥ ጉዳያቸው ጣልቃ ላለመግባት በሶስተኛ ወገኖች ፊት ዋስትና እንዲሰጥ፤

5ኛ. ወደ አገሩ ለስራ ለሚገቡ ሰዎች ዋስትና እንዲሰጥና እረዳችኋለሁ ብሎ ወደ አገሩ ካስገባ በኋላ መዳረሻቸውን ያጠፋቸውን ሰዎች ሁኔታ እንዲገልጽ። ለአብነት ያህልም የኢትዮጵያ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ መሪ የነበረውን ተስፋየ ጌታቸውንና የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ሊቀመንበር የነበረውና ከሻቢያ ፍላጎት ውጭ በከፍተኛ ድምጽ ሁለት ጊዜ የተመረጠውን ኮለኔል ታደሰን የት እንዳደረሳቸው ወዘተ ተጠይቆ አጥጋቢ መልስ እንዲያገኙ። ይህን ማድረግ ካልቻሉ ነገ የነሱም እጣ ፋንታ ያው ነውና።

6ኛ. በማስለጠን፤ በማማከርም ሆነ በሌሎች የቴክኒክ ጉዳዮች ስበብ የሻቢያ ሰዎችን አለመጠቅም፤ በቂ ኢትዮጵያዊ የሰው ሃይል አለና።

7ኛ. ኢትዮጵያን ለማፍረስ በጎሳና በጎጥ እያደራጀ የሚያስታጥቀውን እንዲያቆም ወዘተ በእነዚህንና መሰል ውሳኝ ጉዳዮ ላር መደራደርና መጠየቅ ይጠበቅባቸዋል።

ባጭሩ በኢትዮጵያ ስም ከሻቢያ ጋር የሚደረግ ድርድር ሚስጥር ብሎ ነገር ሊኖረው አይጠበቅም። ያለበለዚያ በውጭም በውስጥም በገጠመው ቀውስ ምክንያት ሊሞት ከሚንጠራወዝ ሻቢያ ጋር ንክኪ ትርፉ የወያኔን ብቻ ሳይሆን የሻቢያን እድሜ ማራዘም ነው።

የኢትዮጵያ አምላክ ይርዳን !
እግዜር ኢትዮጵያን ከጠላቶቿም ከልጆቿም ይጠብቃት !!
ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን (ሱዳን)